**የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በአዲስ አበባ ከተማ ላይ ያለውን ሕገ-መንግስታዊ ልዩ ጥቅም አስመልክቶ የተዘጋጀውን ረቂቅ አዋጅ በሚመለከት የቀረበ መግለጫ**

## 1/ መግቢያ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አገሪቱ ፌዴራላዊ የአስተዳደር ሥርዓትን እንደምትከተል በመደንገጉ ላለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት ዲሞክራሲያዊ የፌዴራል ሥርዓት ለመገንባት የተደረጉ ጥረቶች ጠንካራና በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድነትን በልዩነት ውስጥ ለመገንባት የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ጥረቶችንና ርብርቦሽ እያደረጉ ይገኛሉ።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት ለኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች እውቅና ከመስጠቱም በላይ ጥበቃ አድርጓል።

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ገና ከሕገ መንግስቱ መግቢያ ላይ የገቡት ቃልኪዳን የሕገመንግሥቱን ዓላማ በዝርዝርና በማያሻማ መልኩ ያስቀመጠ ነበር። የኢ.ፌ.ድ.ሪ ሕገ መንግስት የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ በሆነው አገራቸው ላይ ብሩህ ተስፋ ሰንቀው እንደ አንድ ሆነው እንዲነሳሱ የሚያደርጋቸው እውነታዎች የያዘ የሕጎች ሁሉ የበላይ የሆነ የሕግ ሰነድ አላቸው። ኢትዮጵያዊያን በታሪክ ሂደት ውስጥ ያፈሩት የጋራ ሀብት፣ የጋራ እሴትና ትስስር ያላቸው እንዲሁም በዚህ ታሪክ ሂደት ውስጥ የተዛቡ ግንኙነቶች የነበሩና እነዚህ የማይደገሙበትን ሁኔታ የሚፈጥር እንዲሁም በራሳቸው ፍላጎትና በፈቃዳቸው የመሠረቱት የፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሆኑንና ይህ በፈንታዉ ዘላቂ ሰላምን፣ ዋስትና ያለው ዴሞክራሲ እንዲሰፍን እንዲሁም ፈጣንና ሕዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበትን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገትና ብልጽግና የሚያጎናጽፋቸው እንደሚሆን አምነዋል።

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፍላጎት አንድ ጠንካራ የጋራ ኢኮኖሚያዊና ፖሊቲካዊ ማኅበረሰብ በመፍጠር ተወዳዳሪ መሆን በመሆኑ ይህንም በዓለት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን የግለሰብ ወይም የዜግነትም ሆነ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብቶችና የፆታና ሌሎች እኩልነቶች፣ ባሕሎች፣ ኃይማኖቶችና እምነቶች ያለአድሎና ልዩነት እንዲራመዱ ማድረግ ጽኑ እምነታቸው እንዲሆን በቃልኪዳናቸው ሰነድ ላይ አስፍረዋል።

የኦሮሚያ ክልል ሕዝብም ሆነ የኦሮሞ ብሔር አዲስቱ ኢትዮጵያ ግንባታ ላይ ልክ እንደሌሎቹ የኢትዮጵያ ክልሎችም ሆነ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች ሕዝቦች በራሱ ፈቃድና ፍላጎት ይህንን የቃልኪዳን ሰነድ በማጽደቅ መጪው ጊዜ ብሩህ እንዲሆን መታገል ከጀመሩ ይኸው ሁለት አሥርት ዓመታት አልፈዋል። የኦሮሞ ሕዝብም ገና ሕገመንግሥቱ ሲፀድቅ በራሱ ክልል እምብርት ላይ የምትገኘዋን አዲስ አበባን የጋራ ለሆነው የፌዴራል መንግሥት መቀመጫ እንድትሆን በጋራ ወስኗል። ይህም ሆኖ



www.chilot.me

ቀጥሎ በምናያቸው ምክንያቶች ከሌሎች የፌዴራል ሥርዓቱ አባል ክልሎች በተለየ ሁኔታ የኦሮሚያ ክልል ከአዲስ አበባ ሊጠበቅለት የሚገባ ልዩ ጥቅም እንዳለ የኦሮሞን ሕዝብ ጨምሮ ሌሎች የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በጋራ የወሰኑት ጉዳይ ነው፡፡ ይህንንም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ (5) ላይ በማያሻማ ሁኔታ አስፍረውት ይገኛሉ፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ የኦሮሚያ ክልል ብቻ ሳይሆን መላው የፌዴራሉ ሥርዓት አባል ክልሎችም እኩል ተጠቃሚ እንደሚሆኑ በማመናቸው የተቀመጠ ድንጋጌ እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል፡፡

አዲስ አበባ ከተማ በኦሮሚያ ክልል እምብርት ላይ የምትገኝ ነች፡፡ አዲስ አበባ የኦሮሞ አርሶ አደሮች የነበሩባት እና ያሉባት ከተማ እና የኦሮሚያ ክልል ዋና ከተማ በመሆኗ እንዲሁም የአገራችን መዲና ስትሆን አልፎተርፎም የአፍሪካ ፖሊቲካና ዲፕሎማሲያዊ መዲና ናት፡፡ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከኒዮርክና ጀኔቫ ቀጥላ ሦስተኛ ማዕከልም ነች፡፡ የአዲስ አበባ ከተማን ከኦሮሚያ ክልል ጋር የሚያስተሳስሩ በርካታ ተፈጥሯዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ አስተዳደራዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች አሉ፡፡ የአዲስ አበባ ከተማንና ኦሮሚያ ክልልን የሚያስተሳስሩ በርካታ ጉዳዮችን በአግባቡ ለማስተናገድ እና የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ከአዲስ አበባ ከተማ ላይ ያለውን ልዩ ጥቅም መጠበቅ አስፈላጊ በመሆኑ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 5፡

> *"የኦሮሚያ ክልል የአገልግሎት አቅርቦት ወይም የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምና የመሳሰሉትን ጉዳዮች በተመለከተ እንዲሁም አዲስ አበባ በኦሮሚያ ክልል መሀል የምትገኝ በመሆኗ የሚነሱ ሁለቱን የሚያስተሳስሩ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ያለው ልዩ ጥቅም ይጠበቅለታል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡"*

በማለት ይደነግጋል፡፡

የሕገ መንግሥቱን ድንጋጌ በሥራ ላይ ለማዋል እና የኦሮሚያ ክልልን ልዩ ጥቅም ለማስጠበቅ ዝርዝር ሕግ ለማውጣት ጥረቶች ሲደረጉ ነበር፡፡

በረቂቅ አዋጁ ዝግጅት ሂደት ውስጥ የኦሮሚያ ክልል፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች ተሳትፈውበታል፡፡ ረቂቅ አዋጁ በ25 አንቀፆችና በበርካታ ንዑስ አንቀፆች ተከፋፍሎ የተዘጋጀ ሲሆን ያካተታቸው ዋና ዋና ድንጋጌዎችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

## 2/ <u>ክልሉ በከተማው አስተዳድር ስለሚኖረው የማህበራዊ አገልግሎቶች አቅርቦት ልዩ ጥቅም በተመለከተ</u>

ከማህበራዊ አገልግሎቶች ጋር ተያይዞ መመለስ እንዳለባቸው የተለዩት በአፋን ኦሮሞ ትምህርት መስጠት፣ የጤና አገልግሎት ማግኘት፣ ባሕል፣ ቋንቋና ሥነጥበብ መብቶች ጥቅም ማግኘት ሲሆኑ በረቂቅ አዋጁ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

የትምህርት ጥቅምን በተመለከተ በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 4 በመስተዳድሩ ውስጥ ነዋሪ የሆኑ የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች በአፋን ኦሮሞ የሚማሩበት ትምህርት ተቋማት በከተማ



www.chilot.me

አስተዳደሩ ወጪ እንዲደራጁ እንደሚደረግ ተደንግጓል፡፡ ይህ እንዲሆን የተደረገው የአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በርካታ የኦሮሞ አርሶ አደሮች ያሉባት በመሆኑና ከተባበሩት መንግስታት ሦስተኛ ማዕከልነት፣ ከአፍሪካ የፖሊቲካና የዲፕሎማሲ መዲናነትና ከፌዴራሉ መንግስት መቀመጫነት ባሻገር የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት መቀመጫ በመሆኗ ጭምር ነው፡፡

ሌላው የጤና አገልግሎት ጥቅም ሲሆን በረቂቅ አዋጁ በአንቀጽ 5 በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ በሚገኙ ከተሞችና ገጠሮች የሚኖሩ ነዋሪዎች በከተማው ውስጥ በሚገኙ የመንግሥት ሆስፒታሎች እና ጤና ተቋማት የውስጥ አገልግሎት እንደማንኛውም የከተማዋ ነዋሪ ማግኘት የሚችሉበት ሁኔታ እንደሚመቻች ተደንግጓል፡፡ ይህም የሆነበት ዋናው ምክንያት በተግባር በርካታ በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ የሚኖሩ የኦሮሞና የሌሎች ብሔረሰቦች ጭምር አገልግሎት ለማግኘት በብዙ ቁጥር የሚመጡ በመሆኑ ከተማ አስተዳደሩም ለዚሁ አገልግሎት ራሱን በበጀትና በቁሳቁስ አዘጋጅቶ አገልግሎቱን መስጠት ያለበት በመሆኑ ነው፡፡

ሌላው ባሕል፣ ቋንቋና ሥነጥበብ መብቶች ጥቅሞችን በተመለከተ በረቂቂ አዋጁ አንቀጽ 6 ላይ፣

- በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን ልዩ ጥቅም አገልግሎቶችን ለኦሮሞ ብሔር ተወላጆች ለማቅረብ እንዲቻል አፋን ኦሮሞ በከተማ አስተዳደር የሥራ ቋንቋ ሆኖ እንደሚያለግል፤
- የኦሮሞ ሕዝብ ማንነት የሚያንፀባርቅ አሻራ በከተማው ውስጥ በቋሚነት እንዲኖር ከክልሉ ሕዝብ ጋር በተያያዙ ታሪካዊ ክስተቶች ስም መታሰቢያዎች እንዲኖሩ አመቺ የሆኑ እንደ አደባባዮች፣ ጎዳናዎች፣ ሠፈሮች እና የመሳሰሉት ቦታዎች እንደአስፈላጊነቱ በቀድሞ የኦሮሞ ስማቸው እንዲጠሩ እንደሚደረግ፤
- የከተማው መስተዳድር የኦሮሞ ሕዝብ ባህልና ታሪክ የሚያንጸባርቁ ቲያትር ቤቶች፣ የመዝናኛ፣ የባሕል እና የኪነጥበብ ማዕከሎች የሚገነቡበትን የሚተዋዉቁበት ሁኔታዎች እንዲመቻቹ እንደሚያደርግ፤
- በከተማው አስተዳድር ውስጥ በሚገኙ ሙዚየሞች ውስጥ የኦሮሞን ሕዝብ ታሪክ፣ ባሕልና ወግ የሚያንጸባርቁ ቅርሶችና መጽሐፎች እንዲሟሉና እንዲኖሩ አስተዳደሩ ከክልሉ ጋር በመመካከር እንደሚሠራ፤
- በከተማዋ በመንግሥት የሚሰራጩ የመገናኛ ብዙሃን በአፋን ኦሮሞ ጭምር የሚጠቀሙበት ሁኔታ እንደሚኖር፤
- ከኦሮሚያ ክልል ጋር በተያያዘ ከተማው የተቆረቆረበት በአፋን ኦሮሞ የቀድሞ ስሙ ፊንፊኔ አዲስ አበባ ከሚለው የከተማው መጠሪያ ጋር በሕግ ፊት እኩል እውቅና እንደሚኖረውና የስሞቹ አጠቃቀም በተመለከተ ደንብ እንደሚወጣ

ተደርጎ ረቂቁ ተዘጋጅቷል። እነዚህ አገልግሎቶች በልዩ ጥቅምነት እንዲጠበቁ የተቀመጠበት ዋናው ምክንያት ከተማው የተመሠረተበት ታሪካዊ ቦታ በኦሮሚያ ክልል እምብርት ላይ በመሆኑና የኦሮሞ ሕዝብ ከመጀመሪያውም የሚኖርበት አሁንም ሰፊ የኦሮሞ አርሶ አደርን ያቀፈ፣ ከተማዋ የኦሮሚያ ክልል መዲናም ጭምር በመሆኗ ነው። በተጓዳኝ ደግሞ ከተማዋ የዓለም አቀፍ ድርጅቱ ሦስተኛ ማዕከል፣ የአፍሪካ መዲና እንዲሁም ፌዴራል መንግሥቱም መቀመጫ በመሆኗ እነዚህን እውነታዎች ታሳቢ አድርጓል። በዚህም መሠረት የከተማዋ ስያሜ የፌዴራል መንግሥቱና የዓለም አቀፍ ተቋማትን ግንኙነት በተመለከተ አዲስ አበባ የሚለው ስያሜ መቀጠል ያለበት ሆኖ፣ ስትቆረቆር ለነበራት ፊንፊኔ ለሚለው ስያሜዋ እውቅና መስጠት አስፈላጊ በመሆኑና ይህ ስያሜ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት የከተማዋ ስያሜ ሆኖ የሚያገለግል በመሆኑ፣ በተጨማሪም የፌዴራል መንግሥቱና የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ደብዳቤ ልውውጥ የሚያደርጉበትን ሥርዓት በግልጽ ማስቀመጥ በማስፈለጉ ሁለቱም ስያሜዎች በሕግ ፊት እኩል ዕውቅና እንዲኖራቸው በማድረግ አጠቃቀሙ በደንብ እንዲወሰን ተቀምጧል።

## 3/ <u>ክልሉ በከተማው አስተዳድር ስለሚኖረው ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት ልዩ ጥቅም</u>

ክልሉ በከተማው አስተዳድር ስለሚኖረው ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት ልዩ ጥቅም በተመለከተ ከአንቀጽ 7 እስከ አንቀጽ 13 የተደነገገ ሲሆን የመሬት አቅርቦት፣ የውኃ አቅርቦት፣ የትራንስፖርት አገልግሎት፣ የሥራ ዕድል ተጠቃሚነት፣ የገበያ ቦታ አቅርቦት፣ የኮንዶሚኒየም ቤት ተጠቃሚነት፣ ካሣ የማግኘት እና በዘላቂነት የመቋቋም መብት እንዲያካትቱ ተደርጎ ረቂቁ አዋጁ ተዘጋጅቷል።

መሬት አቅርቦትን በተመለከተ ክልሉ ለተለያዩ መንግስታዊ ሥራዎች እና ሕዝባዊ አገልግሎቶች የሚውሉ ሕንፃዎች የሚሠሩበትን መሬት ከሊዝ ነጻ እንዲያገኝ በአዋጁ ውስጥ ተካቷል።

የውኃ አቅርቦት በተመለከተ የከተማው አስተዳድር ከክልሉ ከርሰ ምድርና ገጸ ምድር የሚያገኘው በመሆኑ የመጠጥ ውኃ ምንጭ ጉድጓድ የሚቆፈርበት፣ ግድቡ የሚለማበት፣ ወይም የውኃ መስመሩ አቋርጦ የሚያልፍባቸው የክልሉ ከተሞች እና ቀበሌዎች በአስተዳድሩ ወጪ የመጠጥ ውኃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ በአዋጁ ውስጥ ተካቷል።

ሌላው የትራንስፖርት አገልግሎት የሚመለከት ሲሆን የከተማ አውቶቡስና ታክሲዎች ትራንስፖርት ስምሪት እንዲሁም የባቡር መሠረተ ልማት ዝርጋታና አገልገሎት በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ ያሉትን የክልሉ ከተሞች ያማከለ እንዲሆን ለማድረግ በአዋጁ ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል።

ሌላው ከኢኮኖሚ አገልግሎት ጋር የሚያያዘው የሥራ ዕድል ሲሆን በዚህ ረገድ በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ በሚገኙ የክልሉ ከተሞችና ገጠሮች ውስጥ ነዋሪ የሆኑ

ወጣቶች በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ባለው የሥራ ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችል ድንጋጌ እንዲሁም ከውኃ ልማት፣ ከደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ፣ ከቆሻሻ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት፣ ከተፋሰስ ልማት፣ ከትራንስፖርት አገልግሎት እና ከመሳሰሉት ጋር ተያይዞ የሚፈጠረውን ሥራ ዕድል የክልሉ ከተሞችና ገጠር ነዋሪ ወጣቶች ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሁኔታ እንደሚመቻች ተመልክቷል፡፡

ከአርሶ አደሩ የግብርና ምርት ሽያጭ ጋር በተያያዘ የገበያ ቦታ አቅርቦት ለክልሉ አርሶ አደሮች አስፈላጊ በመሆኑ በተደራጀ መልኩ ምርቶቻቸውን የሚሸጡበትን የገበያ ቦታ እንደሚደራጅላቸው ይህን ደግሞ ከተማ አስተዳደሩ በራሱ ወጪ ተገንብቶ ለግብይት ሥራ ምቹ እንዲሆን እንደሚደረግ በአዋጁ ተካቷል፡፡

የኮንዶሚኒየም ቤት ተጠቃሚነትን በተመለከተ በመንግሥት ወጪ ከሚገነቡ የኮንዶሚኒየም ቤቶች በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ ነዋሪ የሆኑ የኦሮሚያ ክልል መንግሥት ሠራተኞችና ኃላፊዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ኮታ ተሰጥቷቸው በዕጣ ውስጥ የሚካተቱበት የሕግ ሽፋን እንዲያገኝ ተደርጓል፡፡ ይህም በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ እና በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ የራሳቸው ቤት የሌላቸው የኦሮሚያ ክልል መንግሥት ሠራተኞችና ኃላፊዎች ተረጋግተው ሥራቸውን እንዲሠሩ ለማገዝ የሚደረግ አገልግሎት ነው፡፡

ሌላው ካሣ የማግኘት እና በዘላቂነት የመቋቋም መብት የሚመለከት ሲሆን በከተማው ውስጥ በልማት ምክንያት ወደፊት የሚፈናቀሉ አርሦ አደሮች ዘላቂ መቋቋሚያ የሚሆን ካሣ የማግኘት መብት እንዲኖራቸው ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከዚህ በፊት በልማት ምክንያት የተፈናቀሉ እና በቂ ካሣ ያላገኙ አርሦ አደሮች በጥናት ላይ የተመሠረተ የማቋቋሚያ ሥራ እንዲሰራላቸው እና እነዚህ ጉዳዮች የሚመራ ራሱን የቻለ ጽሕፈት ቤት እንዲቋቋም ለማድረግ በሕጉ ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

4/ <u>ክልሉ በከተማው አስተዳድር ስለሚኖረው የተፈጥሮ ሀብት</u> <u>አጠቃቀምና የአካባቢ ጥበቃ ልዩ ጥቅም</u>

በረቂቁ አዋጁ ክፍል አራት የተመለከተው ክልሉ በከተማው አስተዳድር ስለሚኖረው የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምና የአካባቢ ጥበቃ ልዩ ጥቅም ሲሆን ይህም የተፋሰስ ልማትንና ከአካባቢ ብክለት የመጠበቅ መብትን እንዲያካትት ተደርጓል፡፡

የተፋሰስ ልማትን በተመለከተ ለከተማው መስተዳድር የመጠጥ ውኃ አቅርቦት የውኃ ምንጭ የተቆፈረበት፣ ግድብ የለማበት፣ ወይም የውኃ መስመር አቋርጦ የሚያልፍባቸው የክልሉ ከተሞች እና ቀበሌዎች በአስተዳድሩ ወጪ የተፋሰስ ልማት ሊካሄድባቸው እንደሚገባ በአዋጁ ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 92 መንግሥት ሁሉም ኢትዮጵያዊ ንጹህና ጤናማ አካባቢ እንዲኖር የመጣር ኃላፊነት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንጻር ከአካባቢ ብክለት የመጠበቅ መብትን አስመልክቶ፣

- በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ ያሉ ከተሞችና ቀበሌዎች ከከተማው ከሚወጡ ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻዎች ከሚደርሱ የአካባቢ ብክለትና ጉዳት የመጠበቅ መብት እንዳለቸው፤
- ከአዲስ አበባ ከተማ በሚወጡ ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻዎች ከሚደርሱ የአካባቢ ብክለትና ጉዳት የክልሉን ከተሞችና ቀበሌዎች ለመጠበቅ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ እንዲካሄድ እንደሚደረግ፤ በግምገማው መሠረት አስፈላጊው የማስተካከያዎች እንደሚደረጉ፤
- በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ ያሉ ከተሞችና ቀበሌዎች ደህንነቱ ሳይጠበቅና ቁጥጥር ሳይደረግበት ከተቀመጠው ደረጃ በላይ ወደ ክልሉ በተጣሉ ወይም በፈሰሱ ቆሻሻዎች ምክንያት በሰው፣ በእንስሳትና በተፈጥሮ አካባቢ ላይ ለደረሰው ጉዳት በሕግ አግባብ ከአስተዳድሩ ካሳ የማግኘት መብት እንደሚኖራቸው፤
- ለአዲስ አበባ ከተማ ልማት የግንባታ ማዕድናት ማግኛ ሥፍራዎች የአየር ብክለት እንዳያስከትሉ እና ለደን ልማት ወይም ለሌሎች ልማቶች መዋል እንዲችሉ እንዲያገግሙ እንደሚደረጉ፤
- ለአዲስ አበባ ከተማ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ማከሚያና ማስወገጃ ቦታዎች እንዲሁም መልሶ መጠቀሚያ ስፍራዎች አስተዳድሩና ክልሉ በጋራ ባጠኗቸው ቦታዎችና ሳይንሳዊ መስፈርቶችን ባሟሉ ሁኔታዎች እንዲተዳደሩ እንደሚደረጉ፤

በአዋጁ በዝርዝር እንዲካተት ተደርጓል፡፡

5/ __ተቋም ስለማደራጀት__

በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 13 በአስተዳድሩ ውስጥ በልማት ምክንያት የሚፈናቀሉ አርሦ አደሮች ዘላቂ ማቋቋሚያ የሚሆን ካሣ የማግኘት የሚሆን መብታቸውን ለማስከበር እና ከዚህ በፊት በልማት ምክንያት የተፈናቀሉ እና በቂ ካሣ ያላገኙ የኦሮሞ ብሔር አርሦ አደሮች በጥናት ላይ የተመሠረተ የማቋቋሚያ ሥራ ለመስራት ከሚቋቋመው ጽሕፈት ቤት በተጨማሪ አዋጅ ውስጥ የተጠቀሱትንና ሌሎች የጋራ ጉዳዮችን ክልሉ እና አስተዳድሩ የሚወያዩበትና የሚወስኑበት ተጠሪነቱ ለፌዴራል መንግሥት የሆነ ከአስተዳደሩና ከክልሉ ምክር ቤት የተውጣጣ የጋራ ምክር ቤት እንደሚቋቋም ተመልክቷል፡፡

የምክር ቤቱ ዋና ዓላማውም በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 49(5) መሠረት የኦሮሚያ ክልል የአገልግሎት አቅርቦት፣ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምና የመሳሰሉትን ጉዳዮች በተመለከተ፣ እንዲሁም አዲስ አበባ ከተማ በኦሮሚያ ክልል መሀል የሚገኝ በመሆኑ የሚነሱ ሁለቱን የሚያተሳስሩ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ በዚህ አዋጅ የተዘረዘሩትን ልዩ ጥቅሞች በተጨባጭ ተግባራዊ እንዲሆን መከታተል፣ መገምገምና ለአፈጻጸሙ ቅልጥፍና ድጋፍ ማድረግ ይሆናል፡፡



www.chilot.me

የምክር ቤቱን አባላት በተመለከተ ከአስተዳድሩ ምክር ቤትና ከክልሉ ምክር ቤት በእኩል ቁጥር የሚወከሉ እንደሚሆን፤ ዝርዝር የምክር ቤቱ አወቃቀር፣ ተግባርና ኃላፊነት፣ የሥራ ዘመን፣ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት፣ የአባላት ሥነ-ምግባር እና በጀት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣ ደንብ እንደሚወሰን ተመልክቷል፡፡

የረቂቅ አዋጁ ክፍል አራት ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን የያዘ ሲሆን አዋጁንና አዋጁን ተከትለው የወጡ ደንቦችንና ምክር ቤቱ የሚያወጣውን መመሪያና ውሳኔዎች ሥራ ላይ ለማዋል ማንኛውም ሰው ወይም አካል የመተባበር ግዴታ እንዳለበት፤ ከአዋጁ ጋር የሚቃረን ሌላ ማንኛውም አዋጅ ወይም ውሳኔ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት እንደማይኖረው እና ወደፊት አዋጁን በአግባቡ ሥራ ላይ ለማዋል እንዲቻል የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ እንደሚችል እና ምክር ቤቱም አዋጁንና በሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡

## 6/ ማጠቃለያ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ (5) የኦሮሚያ ክልል የአገልግሎት አቅርቦት ወይም የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምና የመሳሰሉትን ጉዳዮች በተመለከተ እንዲሁም አዲስ አበባ በኦሮሚያ ክልል መሀል የምትገኝ በመሆኗ የሚነሱ ሁለቱን የሚያስተሳስሩ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ያለው ልዩ ጥቅም ይጠበቅለታል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል በማለት ይደነግጋል፡፡ የሕገ መንግሥቱን ድንጋጌ በሥራ ላይ ለማዋል እና የኦሮሚያ ክልልን ልዩ ጥቅም ለማስጠበቅ ዝርዝር ሕግ ለማውጣት ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተው ይህ ረቂቅ አዋጅ ሊዘጋጅ ተችሏል፡፡ በረቂቅ አዋጁ ዝግጅት ሂደት ውስጥ የኦሮሚያ ክልል መንግስት፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የመንግስት ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች ተሳትፈውበታል፡፡ አዋጁ እስከሚጸድቅ ባሉ ሂደቶችም ሰፊ የኅብረተሰብ ክፍል ይወያይበታል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተካተቱ ጉዳዮች መሠረቱ ሕገ መንግሥታችንና ምንጩ ከመላው የሀገራችን ሕዝቦች በመሆኑ የኦሮሚያ ክልል ሕዝብ ብቻ ሳይሆን መላው የሀገራችን ሕዝቦች መሆናቸው በውል ተሰምሮበታል፡፡ ይህ አዋጅ በዋናነት የሀገራችን ሕዝቦች ገና በሕገ መንግሥቱ መግቢያ ያስቀመጡትን ዓላማ ለማሳካት ተብሎ የተሠራ መሆኑም ታሳቢ ሊደረግ የሚገባ ነው፡፡ ጉዳዩ የሕዝብ ልዩ ጥቅም በመሆኑ ልዩ ትኩረት የተሰጠው ነው፡፡

በመሆኑም የተከበረው የሚኒስትሮች ምክር ቤት በረቂቅ አዋጁ ላይ ተወያይቶባቸው ከሕገ መንግሥቱ ጋር የተጣጣሙ ስለመሆናቸው ውሳኔ ሰጥቶ አዋጁ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲጸድቅ እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡



www.chilot.me